# ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት አደጋ

ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት መሰረታዊ ትርጉም ለሽብር ተግባራት የሚውል ገንዘብን በመለገስ ድጋፍ ማድረግ ወይም የሽብር ተግብርን የሚያበረታቱ፣ የሚያቅዱ ወይም በሽብር ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን በማንኛውም መንገድ መደገፍ ሲሆን ይህንን ድርጊት በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል።

እነዚህም የሽብር ተግባራትን ለማድረስ የሚያስፈልጉትን ወጪዎች ለመሸፈን የሚውል የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ለምሳሌ የትራንስፖርት ወጪዎች፣ ፈንጂዎችን፣ መሳሪያዎችን እና ተሽከርካሪዎችን ለማግኘት የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚደረጉ የገንዘብ ድጋፎች እና የአሸባሪዎችን ትስስር እንዲሁም የሽብር ተቋማትን እና የህዋሶቻቸውን ህልውና ለመጠበቅ የሚውሉ የገንዘብ ድጋፎችን ማድረግ ናቸው።

ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወይም የመደገፍ ወንጀል በህጋዊ መንገድም ሆነ በህገወጥ የተገኙ ገንዘቦችን በመጠቀም ሊፈጸም ይችላል። በህጋዊ መንገድ የሚገኙ ገንዘቦችን ሽብርተኝነትን በገንዘብ ለመርዳት ዓላማ የሚውሉት በዋናነት ግለሰቦች በሚያደርጓቸው

ልገሳዎች እንዲሁም በህጋዊ መንገድ የተቋቋሙ ድርጅቶች በሚያስገኟቸው ትርፎች አማካኝነት ሲሆን በህገወጥ መንገድ የተገኙ ገንዘቦችን ሽብርተኝነትን በገንዘብ ለመርዳት ዓላማ የሚውሉት እንደ ህገ-ወጥ አደንዛዥ ዕፅ ዝውውር፣ ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር፣ ማጭበርበር እና ውንብድና ካሉ ወንጀሎች የሚገኘውን ገንዘብ በመጠቀም ነው።

ሽብርተኝነትን በገንዘብ ለመርዳት የሚሰበሰቡ ገንዘቦችን የሚጠቀሙ አሸባሪዎች እና አጋሮቻቸው ለዚህ ዓላማ የሚውሉ ገንዘቦችን በተለያየ መንገድ ያዘዋውራሉ።

ከእነዚህም መንገዶች ውስጥ መደበኛ የባንክ አገልግሎት ስርዓቶች፣ መደበኛ ያልሆኑ የገንዘብ ማስተላለፊያ መንገዶች፣ ሀዋላዎች እንዲሁም ጥሬ ገንዘቦችን እና ሌሎች ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎች በማጓጓዣ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ይዞ መሄድ ዋነኞች ናቸው።

ሽብርተኝነትን በገንዘብ ለመርዳት የሚሰበሰቡ ገንዘቦችን ለሽብርተኛነት ተግባር የሚያውሉ ሰዎች ከህግ አስከባሪ አካላት እይታ ራሳቸውን ለመሰወር እና የገንዘብ ለጋሾቻቸው ማንነት እንዳይታወቅ ለማድረግ በህገ-ወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብን ህጋዊ አስመስሎ የሚያቀርቡ ሰዎች የሚጠቀሙባቸውን ዘዴዎች ይጠቀማሉ።

ነገር ግን ሽብርተኝነትን በገንዘብ ለመርዳት ዓላማ የሚደረጉ የገንዘብ ዝውውሮች በህገ-ወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ ለማቅረብ ከሚደረጉ የገንዘብ ዝውውሮች አንፃር በአነስተኛ መጠን የሚደረጉ በመሆኑ እነዚህን የገንዘብ ዝውውሮች መቆጣጠር አስቸጋሪ ነው። ይልቁንም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳቱ ተግባር በህጋዊ መንገድ የተገኙ ገንዘቦችን በመጠቀም በሚሆንበት ጊዜ የገንዘብ ዝውውሮችን የመቆጣጠሩ ሁኔታ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ላይ የሚደርሱ የሽብር ጥቃቶች አፈፃፀም የተወሳሰበ እና በተራቀቀ ሁኔታ የሚፈፀሙ ናቸው።

ከዚህም የተነሳ ለአሸባሪዎች የሚደረገው የገንዘብ ድጋፍ የሽብር ጥቃቶችን ለማድረስ ጉልህ ሚና ይጨወታል።በሽብር ድርጊት ውስጥ የሚሳተፉ ግለሰቦች እንኳን ሳይቀሩ የገንዘብ ድጋፍ ከሌላ የሽብር ድርጊት እንደሌለ ይነገራሉ። በመሆኑም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት የሚያደርሰው ጉዳት የሽብር ድርጊት የሚያደርሰው ጉዳት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

ሽብርተኝነት ከሚያደርሳቸው ጉዳቶች ውስጥ አንዱና ትልቁ በንፁሃን ሰዎች አካልና ህይወት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ነው። ብዙውን ጊዜ የሽብር ጥቃቶች የሚደርሱት ሰዎች በተሰበሰቡባቸው ስፍራ በመሆኑ ሰላማዊ ሰዎች የሽብር ጥቃት ዋነኛ ሰለባ ይሆናሉ፤ ከዚህም የተነሳ አሸባሪነት የሚያደርሰው ጉዳት ዘግናኝ ይሆናል።

አሸባሪዎች የረጅም ጊዜ ዕቅዳቸውን ለማሳከት ከሚጠቀሙባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ በጠላትነት የሚመለከቷቸውን ሀገራት ኢኮኖሚያዊ አቅም ማዳከም ነው። ይህንንም ለማድረግ አገራት በርካታ ገንዘብ አውጥተው የገነቧቸውን ተቋማት እና መሰረተ ልማቶች የሽብር ኢላማ ያደርጋሉ።

በእነዚህ ጥቃቶች የሚደርሰው ውድመትም ምርታማነትን በመቀነስ በአገራቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ጉዳትን ያስከትላል። ከእነዚህ በሰው እና በንብረት ላይ ከሚደርሱ ቀጥተኛ ጉዳቶች በተጨማሪ የሽብር ድርጊቶች ሌሎች ቀጥተኛ ያልሆኑ ጉዳቶችንም በአገር ላይ ያስከትላሉ።

ቀጥተኛ ያልሆኑ ጉዳቶች ውስጥ አንዱ አሸባሪነት የአንድን አገር የኢኮኖሚ ባለድርሻዎች አስተሳሰብ በመቀየር የሚያደረሰው ጉዳት ነው። በአሸባሪነት ምክንያት አለመረጋገት ሲፈጠር ለረጅም ጊዜ በሚቆይ ኢንቨስትመንት መስኮች ላይ የመሰማራት ፍላጎት ስለሚቀንስ የአገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል። በተለይም ሽብርተኝነት የሚፈጠረው አለመረጋገት እንደቱሪዝም ያሉ ኢንዱስትሪዎች ላይ የሚያስከትለው ጫና ጉልህ ነው።

የሽብር ስጋትና ጥቃት ከፍተኛ በሆነ ቁጥር በተለይም በማደግ ላይ ያለው ኢኮኖሚ ያላቸው አገሮች የጎላ ጫና ውስጥ ይወድቀሉ። ችግሩን በአግባቡ በመለየት መግታት ካልተቻለ ደግሞ በአጠቃላይ የአገር ህልውና አደጋ ይሆናል ማለት ነው።

ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት  በንፁሐን ሰዎች አካል መጉደል፣ ህይወት መጥፋት ንብረት መውደም ከመዳረግ በተጨማሪ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ድጋፍ ያደረጉ አካላት ጉዳት ያደርሳል።

ሽብርተኝነትን  በገንዘብ በመርዳት ድርጊት ውስጥ የሚሳተፉ አካላት የህግ ተጠያቂ ይሆናሉ። ተቋማት ከሆኑ ያላቸው መልካም ስም በተጨማሪ ይበለሻል። የዕርዳታ ድርጅቶችም የሽብር ድርጊት ለሚፈፅሙ አካላት መጠቀሚያ ሲሆኑ ያላቸው ክብር እና ተቀባይነት በእጅጉ ይቀንሳል።

ይህን ድርጊት ለማስፈጸም ሌሎችን ያደራጀ ወይም አመራር የሰጠ እንደሆነ፣

ከላይ የተጠቀሱትን ወንጀሎች የሚያቋቋሙ ተግባራትን በመፈፀም የተሳተፈ፣ ለመፈጸም ያደመ፣ የሞከረ፣ የደገፈ፣ ያመቻቸ ወይም እንዲፈፀም ያማከረ እንደሆነ ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀል ተጠያቂ ይሆናል። እነዚህንም ወንጀሎች መፈፀም ከ10 ዓመት እስከ 15 ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት እና እስከ አንድ መቶ ሺ ብር በሚደርስ ገንዘብ መቀጮ ይቀጣል። እነዚህ የወንጀሎች ድርጊቶች በንግድ ወይም በስራ ተግባርነት ተይዘው ከሆነ ወይም የተደራጀ የወንጀል ቡድን ከዓላማዎቹ አንዱ አድርጎት የፈፀመው እንደሆነ ቅጣቱ ከ15 ዓመት እስከ 25 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና እስከ 150 ሺ ብር ሊደርስ በሚችል የገንዘብ መቀጮ ያስቀጣል። የሚመለከታቸው ወይም በህግ ግዴታ የተጣለባቸው አካላት ወንጀሉን ለመከላከል የድርሻቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል። የዓለም አገራትም ሽብርተኝነትን ለመዋጋት የተለያዩ ዓለም አቀፋዊ አገራት እና አገራዊ ህጎችን እያወጡ እና እየተገበሩ ይገኛሉ።